# ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 4 መጋቢት 14 ቀን 2011 ዓ.ም.

## <u>የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት፣ ጠንቅ ለአንድነት</u>

የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ (https://www.youtube.com/watch?v=xcHJfDlj8Xc)

ከሁሉ አስቀድመን ዕሁድ መጋቢት 02 ቀን 2011 ዓ.ም. ወደ ናይሮቢ ኬንያ ለመጓዝ በተነሳ በ6 ደቂቃ ውስጥ በደብረ ዘይት (ቢሾፍቱ) በተከሰከሰው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦይንግ 737 ማክስ 8 አውሮፕላን ሕይወታቸውን ላጡት 149 ተሳፋሪዎችና 8 የበረራው አባላት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን ልንገልጽ እንወዳለን። በአውሮፕላኑ ውስጥ ለነበሩት ሁለቱን አብራሪዎችና ሰባት የበረራው አስተናጋጆችን ጨምሮ ለተለዩን 17 ኢትዮጵያውያን አስደንጋጭ፣ ዘግናኝና መሪር ሀዘን ክብደቱን እየተረዳን ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸውና በዚህ መሪር ሀዘን ስሜታችሁ ለተነካ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ብርታትንና መጽናናትን ታገኙ ዘንድ ከ"***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" እንመኛለን።

ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ችግርና ያልተመለሱ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ለመፃፍ ብዕርና ወረቀት አይበቃም። ታሪካችንና ሂደታችን ቢፃፍ . . . ቢፃፍ የማያበቃ ወራጅ ውኃ ሊመሰል ይችላል። አንዱን አጣጥመን ሰምተን፣ ዓይተን ሳንጨርስ ሌላው ይከተላል። ዛሬማ ከሰዓት በፊት ስላየነው ሳናወራ በፍጥነት አዲሱ ትኩሱ ዜና ይቀየራል። የዛሬ 45 ዓመቱ አብዮት ይህን አሳይቶን አልፏል። የአሁኑ "ለውጥም" ዛሬ የሰማነውን ሳናጣጥም ለሌላ ያስተላልፈናል። ደስ ብሎን ሳንስቅ የሚያስተክዘው፣ የሚያስለቅሰው አየሩን ይሞላዋል። ተለወጠ ብለን ስንጨፍር በአለህበት እርገጥ ያሰኘናል። ታሰሩ ብለን ስንፈነድቅ ተሾሙን እንሰማለን። የኢትዮጵያ አንድነት ብለን ሆ! ስንል ክልላችን ይውጠናል። የምናውለበልበው የአንድነታችን፣ የነፃነታችን፣ የማንነታችን፣ የኢትዮጵያችን ሰንደቅ ዓላማ የተሸከመው ኮከብ ሲያበግነን ቀለማቱን ቀይሮ ምን ታመጣላችሁ? ያሰኘናል።

ለ27 ዓመት በህወሓት ማዕከላዊነት ኢሕአዴግ በሚል የዘር ፖለቲካ የተዋቀረው አገዛዝ ኢትዮጵያን ለመበታተን የቀበረው ፈንጂ ዛሬም መምከን አልቻለም። በአሁኑ ወቅት ኢሕአዴግ ካዋቀራቸው ዘጠኝ ዘርንና ቋንቋን ተገን ካደረጉ ክልሎች ይባስ ብሎ ዛሬ በማንነት ጥያቄ ክልል በክልል ላይ እየተጠየቀ ሀገራችን ልትበጣጠስ እየተንደረደረች ለመሆኑ ወቅታዊ የሀገራችንን ፖለቲካ መቃኘቱ በቂ ነው። ጉዳያችን ስለ ሀገርና ሕዝብ ነውና የግለሰቦችን "ቀና" ንግግርና "ሀሳቢነት" ሳናናንቅ አድምጠናል፣ "ይሁን እስቲ" ብለናል። ቀናት ሳምንታትን፣ ሳምንታት ወራትን፣ ወራት ዓመትን ሲያስቆጥሩ ሂደቶች ሁሉ ወደ ቅስም ሰባሪ፣ አሳዛኝና አደገኛ ሁኔታ እያመሩ ለመሆኑ መገንዘብ አያዳግትም። በዚህ አንድ ዓመት ጉዞ ተፈናቀሉ፣ ተሰደዱ፣ መጠለያ የላቸውም፣ ተቃጠሉ፣ ተገደሉ በየለቱ አየሩን የሞላው፣ የዜና አውታሮች መንደርደሪያ ዜና፣ ድረ ገጾችን ያጣበበ፣ ሶሻል ሚድያዎችን ያጨናነቀ ወሬ ነው።

በዚህ አንድ ዓመት እስከ ሁለት ሚሊዮን የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን በእርስ በርስ ግጭት በየቦታው የተፈናቀሉ እንዳሉ ተዘግቧል። በሶማሊያ ክልል የኦሮሞዎች መፈናቀል፣ ከቤኒ ሻንጉል የተባረሩ የአማራና ኦሮሞ ነዋሪዎች፣ በደቡብ ጌድዮ አካባቢ ከ200 ሺህ በላይ ተፈናቃዮች፣ የወልቃይት አማሮች ጉዳይ፣ የትግራይ ነዋሪዎች መፈናቀል፣ እና ሌላም ሌላ በርካታ ኢትዮጵያውያን ኢሕአዴግ አመጣሹ የዘር ፖለቲካ የፈጠረው የእርስ በርስ ግጭቶች ውጤት ናቸው። በአማራና በትግራይ ክልል አካባቢ ያለው ፍጥጫ፣ የትግራይ ወታደሮች በአማራ ድምበር አካባቢ እየተከማቹ መታየት ሀገሪቷን ወዴት ሊወስዳት እየተንደረደረ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል። ሰፋ አድርገን ስንመለከተው የጉዳዩ መነሻ የዘረኛው ኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ውጤት ነው።

የዛሬ ዓመት አካባቢ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥልጣን ሲረከቡ የኢሕአዴግን ሕገ መንግሥት ተከትዬ ልሠራ ብቻ ሳይሆን ሊያስቀጥሉ እንደመጡ ሲነግሩን "ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ!" የሚለው ድምጽ ብቻ ጋርዶን ላላደመጥነው በዚህ አንድ ዓመት ጉዞ ዛሬ ለተደረሰበት አጠያያቂ ሁኔታ ምንጩ የኢሕአዴግ አገዛዝና ሕገ መንግሥቱ ብቻ ነው። ትላንት ስንታገለው የነበረው ሕገ መንግሥት መሻሻል ሳይሆን መለወጥ አለበት ያልነው ዛሬ በባዶ ጩኸት ኢትዮጵያ ቢባልም ተግባር ላይ ያለው ግና ዘረኛውና ከፋፋዩ ሕገ መንግሥት ነው። "ሕገ መንግሥቱን ተገን አድርገን"፣ "ሕገ መንግሥቱ ተግባራዊ ይሁንልን" ሲባል አዎ! መከፋፈልን፣ መበታተንን፣ መገነጣጠልን አንቀጽ በአንቀጽ አስቀምጦ ይደነግጋልና ሕግን ተገን አድርጎ የመገነጣጠል አባዜን ተግባራዊ ለማድረግ የታቀደ መርዘኛና ሀገር በታኝ ሕገ መንግሥት መሆኑን መረዳት ይገባናል። አሁን አካሄዱ ወደ ዘረኝነት እየተንደረደረ ያለው "ለውጥ አራማጅ" ቡድን የአንድነት ኃይሉን ሀገር ቤት በማስገባትና በማሰባሰብ ይዘን የተነሳነው ሀገራዊና ሕዝባዊ ዓላማ በመዘንጋት የሕገ መንግስቱና የኢሕአዴግ አጫፋሪ ከሆንን በታሪክ ከመጠየቅ አናመልጥም። ወደ ሀገር ገብቶ መታገል ማለት ያለንን የሥርዓት ለውጥና መሠረታዊ ሕዝባዊ ጥያቄ ሊያዘናጋን አይገባም።

በተደጋጋሚ በልሳናችን "***ኢትዮጵያችን***" እንዳስነበብነው የሥርዓት ለውጥ ስንል የኢሕአዴግን አገዛዝ ማብቃት ጨምሮ ዘረኛው የወያኔ ሕገ መንግሥት መለወጥ መሆኑን በድጋሚ ማስገንዘብ እንፈልጋለን። ይህ ሕገ መንግሥት እስካለ ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል አይወገድምና። ኢትዮጵያ 27 ዓመት የተጓዘችበትን ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል እስከቀጠለ ድረስ በሀገራችን እድገትም ሆነ ልማት "ላም አለኝ በሰማይ…" እንደሚባለው ሀሳብና ቅዠት ሁኖ ይቀራል። የዘርና ቋንቋ አከላለል አንዱ ዘር ወደ ሌላው እንዳይገባ፣ እንዳይሠራ፣ የልማት ተካፋይ እንዳይሆን፣ ባህሉን እንዳይጋራ፣ የሃይማኖት ልዩነቱን እንደያዘ እንዳይጓዝ፣ ዘር ለዘር እንደጠላት መተያየትን አብቃይ መሆኑን በአሳለፍነው 27 ዓመት ተመክሮ ካልተማርን የሀገራችን መበታተን መጨረሻው እየዬና ዋይታ እንደሚሆን ከሱማሌ፣ ከሩዋንዳ ሰቅጣጭ ሁኔታ ትምህርት በመቅሰም መጮህና ማልቀስ ያለብን ዛሬ ነው።

በቅርቡ እየተቀጣጠለ የመጣው በአንዳንድ የኦሮሞ ድርጅቶች "አዲስ አበባ የእኛ ነው" ጥያቄ ብቻ ሳይሆን አፈፃጸሙን ለመተግበር ሊኬድበት የሚታሰበው አካሄድ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው። በተደጋጋሚ ብንለውም አሁንም ያለው የሀገራችን ታሪክ ተረት የሆነባቸው፣ ታሪካዊ ቅርሶቻችን ድንጋይ የሆኑባቸው፣ ሰንደቅ ዓላማችን ጨርቅ የሆነባቸው፣ የዓለም ኩራት ዐድዋ "የጡት ቆራጭ" ታሪክ የሆነባቸው፣ አማራን ለማጥፋት ላነጣጠሩ፣ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ምህመናንን ላሰደዱ፤ አዲስ አበባን ፊንፊኔ ቢሉ፣ እናት ሀገር ኢትዮጵያን ዝቅ ቢያደርጉ፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማዋን ቢያቃጥሉ አያስደንቅም። የነሱ ችግር በየጊዜው የተቀያየሩ አፋኝና ጨቋኝ አገዛዞች ሳይሆኑ ኢትዮጵያ በመሆኗ ካልበተኗት፣ ካልገነጣጠሏት ገጀራቸውን ከመሳል፣ ዱላቸውን ከፍ ከማድረግ

*አይመለሱምና። በዘር አመጣሹ አከላለል መሠረት "አዲስ አበባ የእኛ ክልል" ማለት ወያኔ/ህወሓት የቀበረውን የመጨረሻ ፈንጂ በማቀጣጠል ኢትዮጵያን መበታተን መሆኑን ተገንዝበዋልና። ወያኔ በማስፈራራት፣ በድብደባ፣ በአፈና፣ በግድያና በጥይት ጅራፉ 27 ዓመት ፀጥ ለጥ አድርጎ የገዛውን ሕዝባችንን እኛም ዱላና ቆንጨራ አሳይተን አዲስ አበባን እንቀማዋለን ጉዞ የትም እንደማያደርስ ልንጠቁም እንወዳለን።*

*የዛሬ ዓመት እውን ኢትዮጵያ ተዓምር አገኘች፣ መከራ ያልተለየው ሕዝባችን እፎይ ሊል ነው፣ የወጣቶች መንገላታት፣ መታሰር፣ መደብደብ፣ መሰደድ፣ መገደል ሊያበቃ ነው፣ የጀግኖች መኩሪያ የአንድነት ዓርማ ሰንደቅ ዓላማችን ሊውለበለብ ነው፣ ሀገራችን አንድነቷ ሲረጋገጥ፣ ሕዝባችን ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግራይ፣ ጉራጌ፣ አፋሩ፣ ጋምቤላው፣ ወላይታው፣ ሐረሬው ሌላውም ሌላው ሊተቃቀፍ ነው ወዘተ. ብሎ ዳር እስከዳር ደስታቸውን ወጣቶች በጭፈራ፣ እናቶች በእልልታ፣ አባቶች በጭብጨባ፣ ሕፃናት በቡረቃ ያጀቡት የለውጥ ጅማሮ ወደ ትካዜ፣ ሀዘን፣ ቁጭት ተቀይሮ "ምነው ፈጣሪ? መጨረሻችን ምን ይሆን?" ሲያስብል መስማቱና ማየቱ እጅጉን ያማል።*

"***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" *በወቅቱ የለውጡን ሂደት ብንደግፍም ገና ከጅምሩ "የቀን ጅብ በግ ላይሆን . . ."* (http://www.ethiopiachen.org/images/pdf/020511_1H1H-Ethiopiachin-Vol-3-No-1.pdf) *ብለን በኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 1 እትማችን አቋማችንን አሳውቀናል። ኢሕአዴግንና ሕገ መንግሥቱን ይዞ ተፈላጊው ለውጥ ምዕራፍ ላይ እንደማይደረስ በመገንዘባችን በወቅቱ ሰሚ ጠፋ እንጂ አሁንም የሽግግር መንግሥት አስፈላጊነትን ጠቁመናል። የጠቅላይ ሚኒስትር ዶር ዐቢይ አሕመድ እኔ አሻግራችኋለው አባባል የቀን ጅቦችንና ዘረኝነትን አቅፎ እንደማይሠምር ጠቁመን ነበር። ኢትዮጵያን ለመበታተን ተወጥኖ የዛሬ 27 ዓመት በህወሓት ተግባራዊ የተደረገው ሕገ መንግሥት የሀገራችንና የሕዝባችን ህልውና ላይ ያነጣጠረ መሆኑ እየታወቀ ይህን ሕገ መንግሥት ይዞ ለውጥ፤ ዘረኝነትን ከማጠንጠን እንደማይሻገር ዛሬ ላይ ያለውን ወቅታዊ የሀገሪቷን ሁኔታ መቃኘት በቂ ነው።* ***ህወሓት/ወያኔ ሠራሹ የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ለሀገር ሉዓላዊነትና ለሕዝባችን አንድነት ጠንቅ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ከሥርዓቱ ጋር ማብቃት ይኖርበታል።***

"***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" *ለውጥ ስንል የሕዝብ መፈናቀል አይደለም፣ እኛ ለውጥ ስንል ዘርንና ቋንቋን ማዕከል ያደረገ የግዛት አከላለል ያብቃ ነው፣ እኛ ለውጥ ስንል የኢሕአዴግ ሕገ መንግስት መለወጥ ነው፣ እኛ ለውጥ ስንል የዜግነት መብትን ያልገደበ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማለታችን ነው። ይህ ለውጥ ደግሞ አሁንም ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የማህበረሰባዊ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ምሁራን፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካቶ በሚደረግ ምክክርና ውይይት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የአገዛዙን በር ከፈት በማድረግ ነው።*

*በአሁኑ ወቅት እውን ትግራይ በአለው አገዛዝ አስተዳደር ሥር ናትን? በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 መሠረት መገንጠሏ በይፋ አይታወጅ እንጂ የህወሓት ቡድን እንደተቆጣጠራት ግልጽ ነው። የትኛው ክፍለ ሀገር፤ በኢሕአዴግ አባባል የዘር ክልል ነው ሰላም ያለው? "ኦሮሚያ" ሀገርነቱን ለማብሰር የቀረው አዲስ አበባ እንደሆነ እያፈጠጠ መጥቷል። ሲዳማ በመርዘኛው ሕገ መንግሥት መሠረት የራሳቸውን ክልል በማስመር ከደቡብ "ሕዝቦች" ለመለየት አኮብኩበዋል። ምሥራቁ የሀገራችን ክፍል በኦጋዴ ነፃ አውጪ ድርጅት እይታ ሥር ወድቋል። አማራው እራስን በመከላከል የተጀመረው የመደራጀት ሂደት አድማሱን አጥብቦ ለክልሉ መሞገቱን እየታዘብን ነው። አዲስ አበቤዎች ዋናዋን ኢትዮጵያ ባይዘነጉም ያፈጠጠባቸው ዱላና ገጀራ ተሰባስበው ይመክቱት ዘንድ እያስገደዳቸው ይታያል። ይህ ነው እንግዲህ የአንድ ዓመቱ የ"ለውጥ አራማጁ" ስጦታ። እውነት ኢትዮጵያ!*

እንደተባለው ከጅምሩ ዘረኝነትን ከመንከባከብ ይልቅ ጎጂ ጎኑ ላይ ተዘምቶ ቢሆን ሁኔታዎች በመጠኑም ቢሆን እየተቀየሩ በመጡ።

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ኢትዮጵያን ለመበታተን ያሰቡ ኃይሎች ባይሳካላቸውም የእርስ በርስ እልቂት ለመፈጸም ጣታቸው ቃታውን እየሳበ ነው። በየአካባቢው በርካታዎች እየተገደሉ ነው። ከቤት ንብረታቸው እየተፈናቀሉ ለበሽታ፣ ረሃብና ሞት የተዳረጉ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ተበራክተዋል። ቤታቸው በላያቸው ሲናድ፣ ውጡልን እየተባለ ንብረታቸው ሲቃጠል "አላየንም፣ አልሰማንም" እያሉ ዕርዳታ ማሰባሰብ አቁሳይ ጨዋታ ነው። እውን "ለውጥ አራማጅ መንግሥት"፣ ለሀገር አንድነት አሳቢ አገዛዝ፣ ለምስኪኑ ሕዝባችን ተገን ከሆነ ምነዋ! ከቤታቸው ሚፈናቀሉት፣ ንብረታቸው ሚቃጠለው፣ በጥይት ሚቆሉት ጋ ፈጥኖ መድረስ አቃተው? ምነዋ! ሀገር ሰላም እንደሆነች፣ ምንም ኮሽታ እንደሌለ በመፈናቀል አባዜ አውላላ ሜዳ ላይ የወደቁትና እየወደቁ ላሉት፣ በየአካባቢው ላሉ ግጭቶች መፍትሄውን ከመምከር ይልቅ የሰው ድስት ለማማሰል ውጭ ውጪውን ተመልካች ተከነሳ?

በተለይ በአዲስ አበባ አላስፈላጊ ግጭትና መተላለቅ በነዋሪውና በነጣቂዎች እንዳይፈጠር መንግሥትና የአዲስ አበባ አስተዳደር አውቆ መኝታን አቁመው እራሳቸውን መቀስቀስ ይገባቸዋል። በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባና አካባቢዋ ያለውን አለመረጋጋትና ጭንቀት ለመቅረፍም ሆነ የአዲስ አበባን ነዋሪ ለማረጋጋት ቀጥሎ የተመለከቱት ነጥቦች ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ እንጠይቃለን።

1. የከተማዋ ነዋሪ ሰላምና ደህንነት አሳሳቢ ደረጃ ሳይደርስ የህግ አስከባሪና ፖሊስ ኃይል የቅኝትና የጥበቃ ስራውን አጠናክሮ መጀመርና ሁኔታው እስኪረጋጋ መቀጠል አለበት።
2. በ"ሕገ ወጥነት" የተሠሩ ናቸው የተባሉ የመኖሪያና የንግድ ቤቶችን ማፍረስ መቆምና ከአሁን በኋላ ያለፈቃድ የሚሠሩ ቤቶች ላልተወሰነ ጊዜ ማስቆም ያስፈልጋል። ዜጎች ቤት ሰርተው፣ መታወቂያ አውጥተው፣ መብራትና ውሃ አስገብተው፣ ለዓመታት ከኖሩ በኋላ "ሕገ ወጥ" ብሎ ማፍረስ የሕግ አግባብነት የለውም። ኗሪዎችም ሆኑ የከተማ አስተዳደር (መንግሥትመ ቢሆን) በሕግ ፊት እኩል ስለሆኑ ጉዳዩን አግባብ ወዳለው ፍርድ ቤት ወስዶ ከሳሽ የከተማው አስተዳደር ተከሳሽ ነዋሪው ማስረጃና መከራከሪያቸውን አቅርበው ፍትሕ መጠየቅ ይኖርበታል እንጂ የከተማው አስተዳደር እራሱ ከሳሽ፣ እራሱ ምስክር፣ እራሱ ባለማስረጃ ሆኖ የማፍረስ፣ ፍርድ መበየንና ማስፈጸም የዜጎችን ሕጋዊ መብት መጣስ ነው፤ በዚህ መንገድ እየተካሄደ መልካም አስተዳደር አይሰፍንም።
3. ከአዲስ አበባ ለሕዝብ ተወካዮች የተመረጡ እንደራሴዎችና በከተማው አስተዳደር ያሉ የሕዝብ ተወካዮች የሚወክሉት ሕዝብ እየደረሰበት ያለውን የመኖሪያና መነገጃ ቤቶቹ በከተማው አስተዳደር የሚፈርስበትን ተግባር መመርመርና ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ማሳሰባና ሁኔታውንም በቀርብ መከታተል ይገባቸዋል።
4. አዲስ አበባ የፌደራል መንግሥቱና የኢትዮጵያችን ዋና ከተማ ስለሆነች ሁኔታዎች ወደ ሰላምና መረጋጋት እስኪያመሩ ድረስ ማንኛውም የአዲስ አበባ ይገባኛል ጥያቄ ላልተወሰነ ግዜ እንዲቆም ፌዴራል መንግሥቱም ሆነ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መመሪያ መስጠትና ማስፈጸም ይኖርበታል። ዋና ከተማዋ አዲስ አበባን በሚመለከት የሚደረግ የባለቤትነት ጥያቄ እየተከሰተ ካለው የባሰ ውጥረትና የግጭት መንስሔነት አንጻር ማስቆሙ ወቅታዊ እርምጃ ነው።
5. በማንኛውም ጊዜና ቦታ በሚደረጉ "ሰላማዊ" የተባሉ ሰልፎች የሚታዩት መልእክቱን ከሚያስተላልፉ መፈክሮችና ንግግሮች እልፎ ድምጽ አልባም ሆነ ሌሎችን መሣሪያዎች ይዞ መገኘት የፍጥጫ፣ የማስፈራሪያና የሰላም አደፍራሽ ገጽታ በሕግ አስከባሪዎች መከልከል ይገባዋል።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

ኢትዮጵያ ሀገራችን እጅግ የመገነጣጠልና የእርስ በርስ ግጭት ውስጥ ልትገባ እየተንደረደረች ነው። በአራቱም ማዕዘን ያለውን የዕለት ተለት ዘገባ ላደመጠና ለታዘበ የሕዝባችን እየዬ፣ ዋይታ፣ ጩኸት መጨረሻው ጥፋት እንዳይሆን ያሰጋል። በተለያየ ዘመናት ሀገራችንን ያጠቁ የውስጥና የውጭ ኃይሎች እንደነበሩ አንዘንጋ። ዛሬም ይህንን ሊደግሙ ያኮበኮቡ ሀገር በቀልና ባዕዳን ኃይሎችን ጥቃት ልንመክት የምንችለው በጋራ በመምከርና በመደራጀት መሆኑ አጠያያቂ ሊሆን አይገባውም። ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ ሥርዓት ካላበቃ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ከቶም ልትቀጥል አትችልምና መሰባሰቡ ግድ ይላል። በአንዳንድ ዘረኛ ድርጅቶች አቀንቃኝነት አሁን የተያዘው አካሄድ ወገን ከወገን በማጋጨት ሀገራችን ኢትዮጵያን ለመበታተን ነውና በንቃት መከታተል አስፈላጊነቱን ልንጠቁም እንወዳለን። የ27 ዓመቱ የህወሓት/ኢሕአዴግ ሤራ ዛሬ የመጨረሻው ምዕራፍ መደምደሚያ ላይ ደርሷል። ይህ የጥፋት ተልዕኮ ሀገርም ሕዝብም ይዞ እንዳይጠፋ ቁርጠኝነት ይጠይቃልና በጋራ እንነሳ።

***ሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች/ነገዶች ከኢትዮጵያችን የትኛውም ዘር ተገንጥሎ ሀገር መሆን እንደማይችል በመገንዘብ ከአንዳንድ አጥፊ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሰባኪዎች ይልቅ አንድነታችንን በማጠናከር የምንተቃቀፍባት፣ የምንሳሳቅባት፣ የምንኖርባት ሀገራችንን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ መገንባቱ ጠቀሜታው ለኦሮሞው፣ ለትግራይ፣ ለአማራ፣ ለአፋር፣ ለኦጋዴን፣ ለሲዳማ፣ ለወላይታ፣ ለጉራጌ፣ ለጋምቤላ፣ ለሁሉም ጎሳዎች/ነገዶች ነውና "ዘራችን ኩራታችን" ብለን በኢትዮጵያዊነት መንፈስ ሀገራችንን ኢትዮጵያ እናኑራት።***

አዲስ አበባ አይደለም ወለጋ፣ አርሲ፣ ከፋ፣ ኢሉባቡር፣ ባሌ ኦሮሞ የኢትዮጵያ፣ ወልቃይት አይደለም ትግራይ የኢትዮጵያ፣ ቅማንት አይደለም ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎ፣ ሸዋ፣ አማራ የኢትዮጵያ፣ አፋር፣ ኦጋዴን፣ ሐረርጌ፣ አዋሳ፣ ሲዳሞ፣ ገሙጎፋ የኢትዮጵያ ሁላችን ሁላችን ኢትዮጵያ ናት ደማችን። በሀገራችን የመከራችን፣ የድህነታችን፣ የጉስቁላችን ነቀርሳ አምባገነን አገዛዞች እንጂ እምዬ ኢትዮጵያ አይደለችምና አሁንም እንሰዋላት። የሁላችንም እልውና አንዱ ከአንዱ እንደ ሸረሪት ድር የተሳሰረ ነውና አንዱን በጥሰን አብረን እንደምንወድቅ መገንዘብ ይኖርብናል። በሀሰት ቅስቀሳ፣ በ27 ዓመት የዘር ፖለቲካ የተመረዘውን የመገነጣጠል አደጋ ለማንም አይበጅምና "ዘራችን ኢትዮጵያ" ብለን የመነሳቱን ጠቀሜታ ደግመን እናሳስባለን። ከዋርካችን ኢትዮጵያ ተቀንጥሰን የምናተርፈው ኪሳራ ብቻ ሳይሆን በታሪክ ተጠያቂነትን ጭምር ነውና እየከረረ ለመጣው የዘረኝነት ጥፋት በር አንከፈትለት ስንል "***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ድምጻችንን እናሰማለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!
አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ
መጋቢት 14 ቀን 2011 ዓ.ም. (March 23, 2019)

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ስልክ፡ **703 300 4302**
ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin